# ኢትዮጵያ: - የኢትዮጵያ ሰራዊት የኦጋዴንን ነዋሪዎች ይገድላል፣ ያሰቃያል፣ ሴቶችንም እያስገደደ ይደፍራል።

ለጋሽ አገሮች በሰብዓዊነት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን ለማቆም መንቀሳቀስ አለባቸው።

(ናይሮቢ፤ ጁን 12 2008) — የሰብዓዊ መብቶች ታዛቢ (ሂዩማን ራይትስ ዋች) በዛሬው ዕለት ባሰራጨው አዲስ ሪፖርት የኢትዮጵያ ሰራዊት በምዕራብ ኢትዮጵያ የሱማሌ ክልል ከአማጽያን ጋር በሚያደርገው ውጊያ ሰላማዊ ዜጎችን መግደሉን፣ ማሰቃየቱንና ሴቶችንም አስገድዶ መድፈሩን ገልጿል። ይህ ጭካኔ የተሞላበት የመልሶ ማጥቃት ዘመቻ አካል የሆነው ገደብ-የለሽ በደል እየተባባሰ ለሄደው የህዝብ ስቃይ አስተዋጽኦ ያደረገና በሺህ የሚቆጠሩ አርብቶ-አደር ሱማሌዎችን ህልውና አደጋ ላይ የጣለ በመሆኑ ድርጊቱ የጦርነት ወቅት ህግጋትን የጣሰና በሰብዓዊነት ላይ ከተፈጸመ ወንጀል የሚቆጠር መሆኑን ሪፖርቱ ገልጿል።

ይህ "የጅምላ ቅጣት፤ በኢትዮጵያ የሱማሌ ክልላዊ መንግስት ኦጋዴን አካባቢ የተካሄዱ ህገወጥ የጦርነት ወቅት ድርጊቶችና በሰብዓዊነት ላይ የተፈጸሙ ወንጀሎች" በሚል ርዕስ የወጣው 130 ገጽ ሪፖርት በቻይና ዜጎች በሚካሄደው የነዳጅ ፍለጋ ስራ ቦታ ላይ አማፅያን ላደረሱት ጥቃት አጸፋ የኢትዮጵያ ሰራዊት ከጁን 2007 ጀምሮ እያካሄደ ባለው የመልሶ ማጥቃት ዘመቻ በሲቪሎች ላይ የሚፈጸመው ከልክ ያለፈ በደል እየጨመረ መሄዱን ሰንዷል። ይህ የሰብዓዊ መብቶች ታዛቢ ሪፖርት በግጭቱ አካባቢ በኢትዮጵያ መንግስት ጥረት ሳይታወቅ ታፍኖ የቆየውን የግፍና በደል ገጽታ ለመጀመሪያ ጊዜ በጥልቀት አቅርቧል።

በአፍሪካ የሰብዓዊ መብቶች ታዛቢ ዲሬክተር የሆኑት ጆርጄት ጋግኖን ስለ ሁኔታው ሲያስረዱ "የኢትዮጵያ ሰራዊት አማፅያኑን ለመቅጣት ሲል ሰላማዊ ሰዎችን በአሰቃቂ ሁኔታ እያሰቃየ ነው። ይህ በስፋት የተያዘና የተቀነባበረ በደል በሰብአዊነት ላይ እንደሚፈጸም ወንጀል ይቆጠራል። የኢትዮጵያ ዋና ለጋሾች፤ አሜሪካ፣ እንግሊዝና ቤልጅየም ይህንን ወንጀል አላየንም አልሰማንም በማለት የተመሳጠሩ ይመስላል" ሲሉ ገልጸዋል።

በሰብአዊ መብቶች ታዛቢ አጥኝዎች ከመቶ በላይ የሆኑ የስቃይ ሰለባዎችን እና የአይን ምስክሮችን፤ እንዲሁም ነጋዴዎችንና የንግድ መሪዎችን፤ በኬንያ፣ በከፊል ራስገዝ የሰሜን ሱማሌ ምድርና ኢትዮጵያ ያገኟቸውን የክልሉን መንግስት ባለስልጣናት ጭምር አነጋግረዋል። በተጨማሪም፤ መንደሮች በእሳት መቃጠላቸውን የሚያሳይ የሳተላይት ፎቶግራፍ መኖሩ ይህንን በሴፕቴምበር እና ዲሴምበር 2007 በስፋት የተካሄደውን ጥናት ትክክለኛነት የሚያጠናክር ሆኖ ተገኝቷል። በሚዘገንን ሁኔታ ሰዎች በምሽት በጠመንጃ ሰደፍ ሲደበደቡ፤ በአደባባይ ግድያ ሲፈጸም እንደነበርና እንዲሁም መንደሮች በእሳት እንደጋዩ የጥቃቱ ሰለባዎችና ምስክሮች ለሰብአዊ መብቶች ታዛቢ ገልጸዋል።

ሪፖርቱ የኦጋዴን ነፃ አውጭ ግንባር አማፅያን (ኦብነግ) ኦቦሌ በነበረው የቻይና የነዳጅ ፍለጋ ስራ ላይ ኤፕሪል 2007 ጥቃት በማድረስ 70 ቻይናውያንና ኢትዮጵያውን ሲቪሎችን በመግደሉ የኢትዮጵያ ሰራዊት የወሰደውን የአጸፋ ርምጃ አብራርቷል። የመልሶ ማጥቃቱ ርምጃ ተጋግሎ በነበረበት ከጁን እስከ ሴፕቴምበር 2007 የኢትዮጵያ ሰራዊት ጠቅላላውን የገጠር ህብረተሰብ ከስፍራቸው በማስለቀቅ በርካታ የገጠር መንደሮችን እንዳወደመ፤ በዚያውም በኦብነግ ደጋፊነት የተጠረጠሩ ግለሰቦችን ለሌሎች ምሳሌ ይሆናሉ በማለት ቢያንስ 150 ያህል ሲቪሎችን እንደረሸነ፤ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሲቪሎችን በዘፈቀደ ከወታደሮች ካምፕ ውስጥ አስሮ እንደበደበ፤ የአካል ስቃይ፣ አስገድዶ የመድፈርና ሌላም ግብረስጋዊ ጥቃት እንደፈጸመ ምስክሮች ተናግረዋል። በሺህዎች የሚቆጠሩ ሲቪሎች የግጭቱን አካባቢ በመሸሽ ወደ ጎረቤት አገሮች ተሰድደዋል። ከተጠቀሱት የግፍ ምግባሮች ከፊሉ አሁንም እየቀጠሉ ሲሆን፤ የሰብአዊ መብቶች ታዛቢ በዚህ ዘገባ የዘረዘረው የህዝብ በደል ሁሉንም ያካተተ እንዳልሆነ ያምናል።

የኢትዮጵያ ባለስልጣናት የአካባቢ ሚሊሻዎችን ምልመላ በማጣደፍ ያለበቂ ስልጠና ከኦብነግ ጋር እንዲፋለሙ በማድረጋቸው ከፍተኛ የህይወት ጥፋት ደርሷል።

የኦብነግ አማፅያንም ቢሆኑ በኦቦሌ የነዳጅ ስራ ፍለጋ ላይ ባደረሱት ጥቃት በቻይናና በኢትዮጵያውያን ሲቪሎች ላይ እና በመንግስት ደጋፊነት በጠረጠሯቸው ሰዎች ላይ የፈጸሙት ግድያ ከጦር ወንጀል የሚቆጠርና የጦር ወቅት ህግጋትን በማፍረስ በከፍተኛ ደረጃ የሚያስጠይቃቸው ነው።

በግጭቱ አካባቢ የሚኖሩ በርካታ ሲቪሎች ተንቀሳቃሽ አርብቶ-አደሮች በመሆናቸው ለከብቶቻቸው ሳርና ገበያ ፍለጋ ከቦታ ቦታ ይዘዋወራሉ። የኢትዮጵያ ኃይሎች እ.ኤ.አ. ከ2007 ጀምሮ ለኦብነግ አማፅያን የኢኮኖሚ ድጋፍ ለመንፈግ ሲሉ በጦርነቱ በተጎዱ አካባቢዎች ንግድ እንዳይካሄድ፣ ህዝቡ ውሃ፣ ምግብና የግጦሽ ሳር እንዳያገኝ በማድረግ፤ ከብቶቻቸውንና የንግድ ዕቃዎችን በመዝረፍ፤ እንዲሁም ሰብአዊ ርዳታን በማስተጓጎል ተከታታይ ርምጃዎችን ወስደዋል። ይህ “የኢኮኖሚ ጦርነት” በአካባቢው ወትሮውንም የነበረው የዝናብ እጥረት ካስከተለው ድርቅ ጋር ተዳምሮ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎችን አደጋ ላይ የጣለ ሲሆን፤ እስካሁንም መንግስት የምግብ ክፍፍሉን በማቃወሱ በርካታ ሰዎች ምግብ ሊያገኙ አልቻሉም።

ዲሬክተር ጋግኖን ስለሁኔታው ሲገልጹ “መንግስት በሰላማዊ ሰዎች ላይ በሚያደርሰው ጥቃት፣ የንግድ እንቅስቃሴና የርዳታ አቅርቦት በማስተጓጎልም ጭምር በበርካታ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎችን ህግ ጥሶ በጅምላ እየቀጣ ነው። ስለሆነም፤ ሰብአዊ ርዳታ ሰጪዎች በአስቸኳይ ወደ አካባቢው ሄደው የራሳቸውን ግምገማ በማድረግ የምግብ ስርጭቱን ካልተቆጣጠሩት በስተቀር ተጨማሪ እልቂት ይከተላል” ብለዋል።

በግጭቱ የተጎዱ አካባቢዎችን ለመጎብኘት የሰብአዊ መብቶች ታዛቢ ላቀረበው ጥያቄ የኢትዮጵያ መንግስት ምላሽ ካለመስጠቱም በላይ፤ ከአካባቢው የሚመጣውን መረጃ ለማገድ እየሞከረ ነው። ወደ አካባቢው ሄደው የግል ምርመራ ለማድረግ

የሞከሩ ጥቂት የውጭ ጋዜጠኞች በቁጥጥር ስር የዋሉ ሲሆን የአካባቢው ነዋሪዎችና ምስክሮች መረጃ እንዳይሰጡ ተገድደዋል፤ ታስረዋልም። መንግስት በጁላይ 2007 የአለም አቀፍ ቀይ መስቀል ማህበር ኮሚቴን ከሱማሌ ክልል ካባረረ በኋላ የተባበሩት መንግስታትና ሌሎች መንግስታዊ ያልሆኑ ሰብአዊ ርዳታ ሰጭ ድርጅቶችን በጥብቅ ቁጥጥር ስር ተግባራቸውን እንዲያከናውኑ ፈቅዷል።

ይህ የሰብአዊ መብቶች ታዛቢ ሪፖርት የኢትዮጵያ መንግስትና አለም አቀፍ ማህበረሰብ ለዚሁ መፍትሄ ላላገኘ ችግር ያላቸውን ምላሽ ተንትኗል። የኢትዮጵያ መንግስት የቀረበበትን ውንጀላ እየካደ ሳለ የውንጀላውን እውነተኛነት ለማጣራት ግን ምርመራ የማድረግ ፈቃድ የለውም። ለኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ርዳታ የሚያደርጉላት ለጋሽ አገሮች ኢትዮጵያ በአካባቢው የፀረ-ሽብር ጥረት ተባባሪያቸው ብትሆንም፣ የሰብአዊ መብትን በተመለከተ ተጠያቂነት እንዲኖር ለማድረግ አልተጫኑም በማለት የሰብአዊ መብቶች ታዛቢ ወቅሷል። ምዕራባውያን ተቋማት ብቻ፣ አሜሪካ፣ እንግሊዝና ሌሎች የአውሮፓ መንግሰታትን ጨምሮ፣ ለኢትዮጵያ በዓመት ቢያንስ 2 ቢሊዮን ዶላር እርዳታ እየሰጡ፣ ነገር ግን ኦጋዴን ውስጥ ያለውን ከልክ ያለፈ የህዝብ ስቃይና በደል በዝምታ አልፈውታል። ኢትዮጵያን የአካባቢው ፀረ-ሽብር ጥረት ተባባሪ አደርጎ የሚቆጥረው የአሜሪካ መንግስት ወታደራዊ ርዳታውን ጨምሮ ያለውን ተሰሚነት በመጠቀም እነዚህን ወንጀሎች ለማስቆም ግፊት ማድረግ አልፈቀደም።

ዋናዎቹ ለጋሽ አገሮች ኢትዮጵያ ላይ ጫና በማድረግ በደሉን እንዲያስቆሙ የሰብአዊ መብቶች ታዛቢ ቀጥሎ የተዘረዘሩት የመፍትሄ ሃሳቦችን አቅርቧል።

- የአሜሪካ መንግስት በኢትዮጵያ ሰራዊት ስለተፈጸሙ የመብት ጥሰት የተጠናቀሩትን ሪፖርቶች እንዲመረምር፣ የኢትዮጵያ መንግስትም በዚህ ተግባር የተሳተፉ የሰራዊቱን ክፍሎች በመለየት ተጠያቂዎቹን ለፍርድ እስከሚያቀርብ ድረስ፣ አሜሪካ የሰብአዊ መብት ለሚረግጡ የውጭ አገር የጦር ሰራዊት ክፍሎች ርዳታ እንዳይሰት በሚከለክለው የ "ሊሂ ህግ" መሰረት ለኢትዮጵያ ምንም አይነት ርዳታና ስልጠና እንዳይሰጥ፤
- የእንግሊዝ መንግስትና የአውሮፓ ህብረት በበኩላቸው በደሉን እንዲያወግዙና በሱማሌ ክልል እየተፈጸመ ያለውን ወንጀል የኢትዮጵያ መንግስት እንዲያጣራ በይፋ እንዲያሳስቡና በድርጊቱ የተሳተፉ የሲቪልና ወታደራዊ ባለስልጣኖች በሃላፊነት ይጠየቁ ዘንድ ግፊት እንዲያደርጉ፤ ለልማት ስራ የሚሰጥ የገንዘብ ድጋፍ ለደህንነት ስራ ማስፈጸሚያ መዋሉን እንዲቆጣጠሩ ጥሪ ያቀርባል።

ሁኔታውን በተመለከተ ጋግኖን ሲገልጹ፤ "ታላላቅ መንግስታት በመረጃ እጥረትና የእስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ሰበብ በሱማሌ ክልል የሚታየውን የከፋ የሰብአዊ መብት ረገጣ አሳሳቢነት ችላ ብለውታል። ነገር ግን በሰብአዊነት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች እንደዋዛ ሊታዩ አይገባም። በደሉ እስከሚቆምና ወንጀለኞቹም ለፍርድ እስከሚቀርቡ ድረስ ለጋሽ አገሮች በኢትዮጵያ በኩል ያላቸውን ፖሊሲ እንደገና ሊገመግሙት ይገባል" ብለዋል።

በሪፖርቱ በምስክር አንደበት የቀረቡ መረጃዎች፡

"ወታደሮች ላሂሎን በአሳት ካጋዩ በኋላ ወደ አሊን መጡ። ከዚያም አሊንን አቃጠሏት። እኛ በወቅቱ ከዚያው ነበርን። ወታደሮቹ እንደደረሱ ሰውን ሁሉ ከየቤቱ እንዲወጣ አዘዙ። ህዝቡን አንድ ቦታ ሰበሰቡና የሰራዊቱ አዛዥ መንደሩ እንዲቃጠል ትዕዛዝ አስተላለፈ፤ ከዚያም ወደ እኛ ዞሮ 'እነዚህን መንደሮች ለቅቃችሁ ውጡ ብያችሁ አልነበረም?' አለን። ወዲያው ወታደሮቹ ቤቶቹን አቃጠሏቸው። ቤቶቹ የሳር ጎጆዎች ስለነበሩ ባንዳፍታ ጋዩ።"

- የመንደሩ ነዋሪ፤ ሴፕቴምበር 23 — 2007

"ሃሰን አብዲ አብዱላሂ እና አህመድ ጋኒ ጉሌድ ከሚባሉ ሁለት ሰዎች ጋር ተወሰድኩ። በመጀመሪያ ወታደሮቹ በእነዚህ ሰዎች አንገት ላይ ገመድ ከከተቱ በኋላ ከግራና ከቀኝ ሲጎትቷቸው ሁለቱም መሬት ላይ ወደቁ። በዚያ መኻል እኔንም ጉድባ ውስት ከትተውኝ በነበርኩበት አንዱ ወታደር መጥቶ በጠመንጃው ማጽጃ ብረት አንገቴን ሲያንቀኝ ጣቱን ጠምዝዤ አስለቀቅኩት። ከዚያም ሁለት ሌሎች ወታደሮች መጥተው አንገቴ ላይ ገመድ አጥልቀው ይጎትቱኝ ጀመር። ራሴን ከሳትኩበት ነቅቼ ጉድባ ውስጥ መሆኔን እስከማውቅ ድረስ የማስታውሰው ይህንን ነው። ራሴን ሳውቅ ራቁቱን የሆነ ሰው እኔ ላይ ተደርቦ ወድቋል። ለካስ አህመድ ጋኒ ጉሌድን ገድለው ከበላዬ ጥለውታል። አንዲት ውሃ ልትቀዳ ስትሄድ የነበረች ሴት እስከምታገኘኝ ድረስ ከጉድባው መውጣት አልቻልኩም ነበር።"

- ሪድዋን ሃሰን ሳሂድ፤ ኦክቶበር 30 — 2007

"በ ኤኬ 47 ጠመንጃ ሰደፍ ደበደቡኝ። ፊቴን በሰደፍ ሲመቱኝ ጥርሴ ተሰበረ። ከዚያም በሰንሰለት ጀርባየንና እግሬን ይገርፉኝ ጀመር። ለአንድ ሰዓት ያህል አሰቃዩኝ። ቀጥሎም ሁለቱንም እግሮቼን አስረው ዘቅዝቀው ከጣራ ላይ አንጠለጠሉኝና 'ተናዘዝ" እያሌ ገረፉኝ። ለሁለት ወራት ከየታሰርንበት እየተወሰድን ተገረፍን፤ ተሰቃየን።"

- የሰላሳ አንድ ዓመት ባለሱቅ፤ ሴፕቴምበር 20 — 2007

"እኛን ለማሸማቀቅ ፈልገው የኦብነግ ደጋፊ ያሏቸውን ሁለት ሴት ልጆች አመጧቸው። ሁላችንም እንድንመለከት ከፊታችን ረሸኗቸው። በመጀመሪያ 'የምታውቁትን ካልነገራችሁን ትደገላላችሁ' አሏቸው። ከዚያም ሁለቱንም በጥይት መቷቸው። ሟቾቹ ልጃገረዶች ተማሪዎች ነበሩ። ስማቸውም ፋዱማ ሃሰን፤ ዕድሜ 17 እና ሳምሳም ዩሱፍ፤ ዕድሜ 18 ነበር።"

- ተማሪ፤ ሴፕቴምበር 23 — 2007

"በቆራሌ በሸቦ የታጠረ የውሃ ጉድጓድ አለን። የኢትዮጵያ ሰራዊት የጉድጓዱን ውሃ እንዳንጠቀም ስለከለከለን ሌሊት ተደብቀን መሄድ ነበረብን። ይህ ሁሉ ግፍ የደረሰብን ዘንድሮ ነው። በሌሊት ሄደን ውሃ እያመጣን ቤታችን ለማጠራቀም እንሞክራለን። ነገር ግን ወታደሮቹ ውሃ ስንቀዳ ካዩን ሊገድሉን ይችላሉ።"

- የመንደሩ ነዋሪ፤ ሴፕቴምበር 23 — 2007

“የፌዴራል መንግስት ህግን ተከትሎ ቢሰራ ጥሩ ነበር፤ ነገር ግን ራሱ ያወጣውን ህግ ሊያከብር አልቻለም።”

- የቀድሞ የክልል ፍርድ ቤት ዳኛ፤ ዲሴምበር 5 — 2007

**“የጅምላ ቅጣት፤ በኢትዮጵያ የሱማሌ ክልላዊ መንግስት ኦጋዴን አካባቢ የተካሄዱ ህገወጥ የጦርነት ወቅት ድርጊቶችና በሰብዓዊነት ላይ የተፈጸሙ ወንጀሎች” በሚል ርዕስ የሰብአዊ መብቶች ታዛቢ ያወጣው ዘገባ በሚከተለው በሚከተለው ድህረ ገጽ ይገኛል**

http://hrw.org/reports/2008/ethiopia0608/